በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የየካ ክፍለ ከተማ ት/ፅ/ቤት የ6ኛ ክፍል ሞዳል ፈተና

አማርኛ, 2016 ዓ.ም/ 2024 እ.ኤ.አ

የጥያቄ ብዛት: 40 የተፈቀዮው ሰዓት: - 1 ሰዓት

አጠቃሊይ ትዕዛዝ

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋሌ፤ ለእያንዱንደ ጥያቄ ትክክለኛ መሌስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ የመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ሊይ በመፃፍ መሌስ ይሰጣሌ፡፡ በፈተና ሊይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋሌ፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመሌስ መስጫ ወረቀት ሊይ ነው ፤በመሌስ መስጫው ሊይ ትክክለኛውን መስስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በመፃፍ ሲሰራ ለመፃፍ የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መሌኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መሌስ ለመቀየር ቢፈሇግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዲት አለበት፡፡ ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዳት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ዴረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡ መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዱይፈተንም ይደረጋሌ፡፡ ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመሌስ መስጫው ሊይ መሞሊት የሚገባውን መረጃ ሁለ በጥንቃቄ መሞሊት አለበት፡፡

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባሌ መጀመር አይፈቀድም !



LIVEWORKSHEETS

***መመሪያአንድ ፡-*** ከተራ ቁጥር 1 -5 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች ምንባቡ መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው ። ስለሆነም ምባቡን በጥሞና በማናበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከተሠጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ መስጫውላይ አጥቁሩ፡፡

የሀገራችን ወንዞች በአራት ዋና ዋና መደቦች ይከፈላሉ፡፡ የመጀመሪያ መደብ ተከዜን፣ አባይን እና ባሮን ያቀፈ ሲሆን እነሱንም አንድ የሚያደርጋቸው በሙሉ ወደ ምዕራብ ፈሰው ከትልቁ የአባይ ወንዝ ጋር መገናኘታቸው ነው፡፡ከነዚህ ከሶስቱ በጣም ዝቅተኛ የሆነው አባይ ነው፡፡በአወንታዊውም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ብዙ ዘፈኖች ተደርሰውለታል፡፡ የተለያ ተረቶችና ወጎችም እነሱን መነሻ አድርገውታል፡፡ ምንጨን የጣና ሐይቅን ለማግኘትም አያሌ የውጭ ዜጎች ለዘመናት ዳክረዋል፡፡ ሁለተኛው መደብ ገናሌንና ዋቢሸበሌን ያቀፈ ሲሆን ሁለቱም ወንዞች ወደ ህንድ ውቅያኖስ የሚፈሱ ናቸው፡፡ ሶስተኛ ሰው መደብ መነሻው ላይ ጊቤ ወረድ ሲል የሚገኘው ኦሞ ተብሎ የሚታወቀው ወንዝ ሲሆን ኢትዮጵያንና ኬንያ ወሰን ላይ ወደ ሚገኘው የቱርካና ሩዶልፍ ሀይቅ ይፈሳል፡፡በአራተኛው የወንዝ መደብ የሚገኘው ደግሞ ማዕከላዊ የሆነ አዋሽ ሲሆን ከምዕራብ ሸዋ ተራሮች ተነስቶ የሚሄድበትን ያጣ ይመስል ከባዘነ በኋላ የስምጥ ሸለቆን እያረሰ አፋር በረሀ ሲደርስ አሸዋ ውስጥ ባክኖ ይቀራል፡፡

ምንጭ፡- 2007 ከታተመው ከአማርኛ 5ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ላይ የተወሰደ፡፡

፩• ከላይ የቀረበው ምንባብ ከድርሰት አይነቶች ውስጥ በየትኛው የድርሰት አይነት ይመደባል?

ሀ/ በገላጭ ድርሰት ለ/ በተራኪ ድርሰት ሐ/ በአመዛዛኝ ድርሰት መ/ በስዕላዊ ድርሰት

፪• የድርሰቱ ሀይለ ቃል በፅሁፉ በየትኛው ክፍል ይገኛል ?

ሀ/ መጀመሪያ ለ/ መካከል ላይ ሐ/ መጀመሪያና መጨረሻ መ/ መጨረሻ ላይ

፫• በድርሰቱ ውስጥ ስንት ወንዞች ተጠቅሰዋል?

ሀ/ ስድስት ለ/ ሰባት ሐ/ አራት መ/ ስምንት

፬• ፀሀፊው በሶስተኛ መደብ የገለፀው ወንዝ የትኛውን ነው?

ሀ/ አባይ ለ/ ጊቤ ሐ/ አዋሽ መ/ ኦሞ

**፭• ወሰን** የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ ያለው አውዳዊ ፍቺ --------------- ነው፡፡

ሀ/ ግንብ ለ/ ቤት ሐ/ ድንበር መ/ አጥር

***መመሪያ ሁለት***፡- ከተራ ቁጥር 6- 25 ለቀረቡት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ተብሎ ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ይበልጥ መልስ የሚሆነውን በመምረጥ መልሱ፡፡

፮• በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ሆኖ የሚያገለግለው የቃል ክፍል ምን ይባላል?

ሀ. ስም ለ. ግስ ሐ. ሀረግ መ. ቅፅል



LIVEWORKSHEETS

፯• በአለም የታወቁና እጅግ የተከበሩ ኢትዮጵያዊ ሰአሊ አፈወርቅ ተክሌ በስሜን ሸዋ አንኮበር ከተማ ጥቅምት 1929 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ በህፃንነቱ እድሜያቸው ኢትዮጵያ ከጣልያን ጋር የነበራትን ጦርነት የተመለከቱ ሰው ናቸው፡፡ ይህ አንቀፅ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ይሆናል፡፡

ሀ. አከራካሪ ለ. ተራኪ ሐ. አስረጂ መ/ ስዕላዊ

፰• ቃላትን አሳጥሮ ለመፃፍ የሚያገለግለው ስርአተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. ይዘት ለ. ህዝበር ሐ. ቅንፍ መ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው

፱• ፈሪ ጨነቀው ተርበደበደ

ጥይት ዘነበ እሳትወረዳ

ሙረድ እንውረድ ተባባሉና

አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና፡፡ ይህ ስነ ቃል ዘርፍ ለየትኛው ተስማሚ ይሆናል?

ሀ. ለፉከራ ለ. ቀረርቶ ሐ. ለሙሾ መ. እንጉርጉሮ

፲• ከሚከተሉት ውስጥ ባለንብረትን አመልካች ቅጥያን የያዘው የትኛው ነው?

ሀ. ደብተርሽ ለ. በሬዎች ሐ. ዘመናዊ መ/ ልባም

፲፩• እኛ ለጉብኝት ጉንደር ሄደን ነበር፡፡ የሚለው ዓ.ነገር የትኛው የጊዜ አይነት ይገልፃል?

ሀ. የሀላፊ ጊዜ ለ. የትንቢት ጊዜ ሐ. የአሁን ጊዜ መ. የወደፊት ጊዜ

፲፪• ከሚከተሉት መካከል የአንቀፅ ባህሪ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አንድነት ለ. ውህደት ሐ. አፅኖት መ. ሁሉም መልስ ነው

፲፫• ከሚከተሉት ቃላት መካከል የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. እነዚህ ለ. ክፉኛ ሐ. ዘንድሮ መ. በፍጥነት

፲፬• ስለ አስተዋፅኦ ወይም ቢጋር መንደፍ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የሃሳብ ድግግሞሽን ለማስቀረት ለ. የሃሳብ ድግግሞሽ እንኖር ማድረግ

ሐ. የሃሳብ ፍሰትን ለመጠበቅ መ. የይዘት ቅደም ተከተልን ለመጠበቅ

፲፭• <u>**ጥሮ ግሮ**</u> ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺው ----------- ነው፡፡

ሀ. ለፍቶ/ ደክሞ ለ. ሳይደክም / ሳይለፋ

ሐ. ሰርቶ/ ተፍጨርጭሮ መ. ጠርጎ/ ጠራርጎ

፲፮• ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ማዳመጥ ለ. መፃፍ ሐ. ማንበብ መ. ማየት

፲፯• ጠንክሮ የሚያጠና **ተማሪ** ውጤታማ ይሆናል፡፡ ተማሪ የሚለው ቃል ከየትኛው ስም ይመደባል?

ሀ. የተፅኦ ለ. የወል ሐ. የረቂቅ መ. የግእዝ

፲፰ ከሚከተሉት መካከል አንዱ ነፃ ምዕላድ ነው?

ሀ. ቤት ለ. ቃላት ሐ. መፅሀፎ መ. ቦርሳው



LIVEWORKSHEETS

፲፱• **<u>ወዳጅነታቸውን</u>** የሚለው ቃል በምዕላድ በትክክል ተነጣጥሎ ሲፃፍ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወዳጅ - ነት - ኣቸውን ለ. ወዳጅነት - ኣቸው - ን

ሐ. ወዳጅ - ነት - ኣቸው - ን መ. ወዳጅ - ነት - ኦቸው - ን

፳• እግረኞች ለእግረኛ ተብሎ የተዘጋጀ መንገድ ካለ በዚያ **<u>መጠቀም</u>** ይኖርባቸዋል። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው ---------------- ነው።

ሀ. መቀመጥ ለ. መስራት ሐ. መሄድ መ. መቆም

፳፩• **<u>ተደናገሩት</u>** በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ባለቤት ማነው?

ሀ. እናንተ ለ. እነሱ ሐ. እሱ መ. እሷ

፳፪• አንድ አረፍተ ነገር ነጠላ ወይም ውስብስብ የምንለው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. በሚይዘው የግስ ብዛት ለ. በሚይዘው የባለቤት ብዛት

ሐ. በሚይዘው የስም ብዛት መ. በሚይዘው የቃል ብዛት

፳፫• ትርጉም አዘል የሆነ የመጨረሻ የቋንቋ ንዑስ ክፍል ነዉ

ሀ. ግስ ለ. ተውሳከ ግስ ሐ. ምዕላድ መ. ስም

፳፬• በትክክለኛ ሰዋሰዉ የተፃፈ አ/ነገር የቱ ነዉ?

ሀ. በግጥም ዉድድር ሞባይል አሸንፋ ተሸለመች።

ለ. ለሞባይል ውድድር አሸንፋ ግጥም ተሸለመች ።

ሐ. በግጥም ውድድር አሸንፋ ተሸለመች ሞባይል ።

መ. በግጥም ውድድር አሸንፋ ሞባይል ተሸለመች።

፳፭• ጓደኛዬ ደስተኛ ነው። ደስተኛ በሚለው ቃል ውስጥ ጥገኛ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ደስታ ለ. ኧም ሐ. ኧኛ መ. ደስተኛ

፳፮• ከሚከተሉት ስርዓተ ነጥቦች መካከል ወይም የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባው የቱ ነው?

ሀ. እዝባር ለ. ትምህርተ ጥቅስ ሐ. ቅንፍ መ. ነጠላ ሰረዝ

፳፯• ጥገኛ ምዕላዶች ከአገባብ አንፃር በስንት ቦታ ሊገቡ ይችላሉ?

ሀ. በመጀመሪያ እና በመጨረሻ ለ. መጀመሪያ፣ መሀልና መጨረሻ

ሐ. መሀላይ ብቻ መ. መጨረሻ ላይ

፳፰ የመኮንን ባህሪ መሬት ነው። የተሰመረበት ቃል ፋካሬያዊ ፍቺ

ሀ. ምድር ለ. ነጭናጫ ሐ. ታጋሽ መ. ለፍላፊ

፳፱• ሲሮጡ የታጠቁት --------------- ይህን ተርትና ምሳሌ የትኛው ሊያሟላው ይችላል?

ሀ. ሲሮጡ ይፈታል ለ. እያደር ይጠብቃል

ሐ. እየላላ ይሔዳል መ. መንገድ ላይ ይወድቃል



LIVEWORKSHEETS

፴• ከሚከተሉት ተዉሳከ ግሶች መካከል ልዩ የሆነው -------------- ነው፡፡

ሀ. ክፉኛ ለ. ባለፈው አመት ሐ. ትላንት መ. አሁን

መመሪያ 3- ከተራ ቁጥር 31-34 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል በትርጉም ልዩ የሆነውን ቃል ምረጡ፡፡

፴፩• ሀ/ አማረረ ለ/ አመሰገነ ሐ/ አሞገሰ መ/ አወደሰ

፴፪• ሀ/ ቆንቋና ለ/ ስስታም ሐ/ ንፉግ መ/ ልግመኛ

፴፫• ሀ/ ችግር ለ/ እንቅፋት ሐ/ ድፍረት መ/ ማነቆ

፴፬• ሀ/ ጎመጀ ለ/ ቋመጠ ሐ/ ጓጓ መ/ መታ

መመሪያ 4- <u>ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ከተጠቀሱት አማራጮች መካከል ተቃራኒ ፍቻቸው በመምረጥ መልሱ፡፡</u>

፴፭• ህቡዕ

ሀ. ድብቅ ለ. ገሀድ ሐ. ስውር መ. የማይታይ

፴፮• ላመ

ሀ. ደቀቀ ለ. ተሰረቀ ሐ. ተሸረከተ መ.በተነ

፴፯• ልባም

ሀ. ቁምነገረኛ ለ. ቀልበቢስ ሐ. ልግመኛ መ. ክብረቢስ

መመሪያ 5- <u>ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ከተጠቀሱት አማራጮች መካከል ተመሳሳይ ፍቻቸው በመምረጥ መልሱ፡፡</u>

፴፰ •ማስተካከል

ሀ. ማነፅ ለ. ማቃናት ሐ. መግራት መ. ሁሉም

፴፱• ሁከት

ሀ. አምባጓሮ ለ. ሰላም ሐ.ፍቅር መ.ፍትህ

፵• ደራ

ሀ. ኮራ ለ. ሰፋ ሐ. ሞቀ መ. ተኮሰ



LIVEWORKSHEETS